# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 56 ሰኔ 4 2001 ዓ.ም


"ይህ ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ በግራም በቀኝም በዚህ ምክር ቤት ውስጥ የተቀመጥን ሰዎች ይህንን ሕግ መቃወም አለብን፣ ምክንያቱም አገራችንን ለአምባገነኖች፣ ለጐበዝ አለቆችና ለፖሊስ ልናስረክብ ነው"

የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ

"እንደውም ረቂቅ አዋጁ ራሱ ሽብር ነው"

የተክበሩ አቶ ወንድሙ ኢብሳ

"የህጎች ሁሉ የበላይ ነው የተባለለት ሕገ-መንግስት በአዋጆችና ድንጋጌዎች ተሸርሽሮ አጥንቱ ብቻ በቀረበት ባሁኑ ወቅት እስከነአካቴዉ ገድሎ የሚቀብረው "የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ" ተረቆለት ለመጽደቅ የጣት ቆጠራ ብቻ ቀርቶታል፡፡ "

ርዕስ አንቀጽ

## በመንግስት ግልበጣ የተያዙት 46 ሰዎች ባለሥልጣኖችን በመግደል ሙከራ ተከሰሱ

ከአንድ ወር በፊት መንግስት በመገልበጥ ሙከራ ክስ ወደ አርባ የሚጠጉ ሰዎችን ማሰሩን እና የነዚህን ሰዎች እቅድ ከጅማሬው ሲከታተለው እንደነበር የተናገረው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ቆየት ብሎ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ሳይሆን ባለስልጣኖችን የመግደል መከራ ሲያቀነባበሩ ነበር በማለቱ በሰጠው እርስ በርሱ የሚጋጭ መግለጫ መሳቂያ መሳለቂያ ሆነ እንደሰነብተ በተለያዩ ሚዲያዎች መዘገቡ ይታወሳል፡፡ ወያኔ በራሱ ሚዲያ በሰጠው በዚህ መግለጫ 'ላለፉት 18 አመታት በወያኔ አድሎአዊ አገዛዝ የተማረረው ህዝብ "አበጁ ምነው ፈጣሪ ቀንቶአቸው ዕድሜህን አሳጥረውልኝ በነበረ" ብለው መፈንደቃቸውን በመገንዘቡ ወዲያው ሳምንት ባልሞላ ጊዜ በተለመደው የቅጥፈት አሰራሩ ኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት መገልበጥ በፍጹም እንደማይቻል እና ሙከራው የመንግስት ባለስልጣናትን መግደልና የህዝብ ንበረት የሆኑትን ተቋማት ማውደም ነበር በማለት ውዥንብር ወደመንዛት ስራው ተመልሶአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአገሪቱ ውስጥ በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ባለሃብቶች ለወያኔ ታማኝነት ያላቸው የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ ተገለጸ

የመከላከያ ሰራዊት ቁልፍ የአዛዥነት እና የመምሪያ ሀላፊነትን በጠቅላላ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ የትግራይ ተወላጆች እንደተቆጣጠሩት ሁሉ የኮንስትራክሽን ዘርፉንም በሚያስገርም ሁኔታ የትግራይ ተወላጆች በሞኖፓል መያዛቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ አንድ መረጃ አመለከተ።እንደ ደረሰን መረጃ በሀገሪቱ ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ፈቃድ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ለአንድ ዘውግ አባላት የተሰጠ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ ውስጥ በስራ ላይ ካሉ የኮንስትራክሽን እንቅስቃሴዎች 60 በመቶ ያክሉ የመንግስት ፕሮጀክቶች በመሆናቸው ፕሮጀክቶቹን ወያኔ ከእኔ ዘውግ መጡ ለሚላቸው ኮንትራክተሮቹ ካለምንም ሀፍረት በጅምላ እንደሚሰጥ ተመልክቷል። በወያኔ እገዛ እና ድጋፍ የተቋቋሙት ኮንትራክተሮች የኢጋዚ እርኩስ ጥይት እንደ ነቢዩ አለማየሁ ያሉ የአስራ አምስት አመት ተማሪዎችን ከፈጀ በኋላ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትን ወደ ዝዋይ የማሰቃያ ካምፕ ሲወስድ የመኪና እርዳታ አድረገው እንደነበር ይታወሳል።አንዱ በአንዱ ላይ እንደ ዶሮ ተጨናንቆ እና ተፋፍጎ የተጫነበትን ገልባጭ መኪና ሳትኮን እና ሰላም የተባሉ የትግራይ ተወላጆች በባለቤትነት የያዙዋቸው የኮንስትራክሽን ድርጅቶች እንደ ሰጡ በወቅቱ በግፍ ዝዋይ ታስረው የነበሩት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ማጋለጣቸው ይታወቃል።አቶ አንዳርጋቸው ከሶስት አመት በፊት ለአሜሪካ ምክር ቤት በሰጡት የምስክርነት ቃል ከአዲስ አበባ በግፍ የታፈሱ ዜጎችን እንደ እንስሳ የተጫኑበትን የጭነት መኪናዎች በጠቅላላ የሰጡት የአንድ ዘውግ አባላት የሆኑ ኮንትራክተሮች እንደሆኑ መናገራቸው አይዘነጋም። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አሸባሪ የሆነው የነመለስ ቡድን በፀረ-ሽብር ሽፋን ያረቀቀው "አሸባሪ ህግ" ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው።

የምስራቅ አፍሪቃ ቀንደኛ አሸባሪ የሆነው የመለስ አገዛዝ፤ እየተጋጋመ የመጣበትን ህዝባዊ ተቃውሞ በህግ ሽፋን ለመግታት በማሰብ በፀረ-ሽብር ሽፋን ያረቀቀው "አሸባሪ ህግ" በአገር ውስጥም ሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው።

ይኸው ረቂቅ ህግ ተብየው ከትናንት በስቲያ በፓርላማው ሲቀርብ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፡- "ሕመንግሥቱን የሚጥስ፣ ዜጐችን ለድብደባ የሚያጋልጥ፤ የአስፈጻሚውን ጡንቻ የሚያዳብርና ራሱ አሸባሪ የሆነ ሰነድ ነው" በማለት ክፉኛ ተቃውመውታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

## የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ግንባር አንድነት ተጋድሎ በሰሜን ሸዋ አካባቢ ባደረሰው ጥቃት ውጤት አስመዘገበ

የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክረሲያዊ ግንባር ግንቦት 14፣ 2001 ዓም በሰሜን ሸዋ የይፋት ከተማ በሰነዘረው ድንገተኛ ጥቃት አርኪ ውጤት ማግኘቱን ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መግለጫ አስታወቀ።

የተንቀሳቃሽ አርበኛ ቁጥር 60 ተብሎ የተመደበው ቡድን በይፋት ከተማ ከምሽቱ 5 ሰአት እስከ ምሽቱ 8፡30 ባደረሰው ጥቃት አካባቢውን ለተወሰኑ ሰአታት መቆጣጠሩንና ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ ማግኘቱን በመግለጫው ላይ አትቷል። ግንባሩ አካባቢውን ከተቆጣጠረ በኋላ ለግንባሩ ድጋፍ አድርገዋል የተባሉ ፖሊሶች መያዛቸውን መግለጫው አመልክቶ፣ የወያኔው አገዛዝ በተፈጠረው ድንገተኛ ጥቃት በመደናገጡ ጦሩን ወደ አካባቢው በፍጥነት ማዝመቱንም ገልጿል። የአካባቢው ህዝብም ከምሽቱ 3 ሰአት በሁዋላ እንዳይዘዋወር የሰአት እላፊ ድንጋጌ መጣሉን ግንባሩ አክሎ ገልጿል።

ግንባሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ ህዝባዊ ተቀባይነቱ እየጨመረ በመምጣቱ ስጋት ላይ የወደቀው የወያኔ አገዛዝ፣ ከግንባሩ ጋር ንክኪ አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ በርካታ ሰዎችንም እያሰረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው የሚገኙ ገበሬዎችም በብዛት ግንባሩን በመቀላቀል ላይ መሆናቸውንና ትግሉን እያጠናከሩት እንደሚገኙ ከስፍራው የሚላኩልን ደብዳቤዎች ያመለክታሉ።

በኢትዮጵያ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ በመምጣቱ ድንጋጤ ውስጥ የገባው ወያኔ፣ ሰሞኑን በሽብረተኝነት ስም የይስሙላ ህግ ለማውጣት የተገደደው እንዲህ አይነቱን ተቃውሞ ለማፈን በማሰብ መሆኑን በርካቶች ይስማሙበታል።

## መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓም የተፈጸመው ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ 4ኛ አመት ታስቦ ዋለ

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የህዝብን ድምጽ በመዝረፍ በስልጣን ላይ ለመቆየት መወሰኑን ተከትሎ የተነሳውን ህዝባዊ ቁጣ ለማኮላሸት ባስወሰደው እርምጃ በርካታ ህጻናት፣ ወጣቶችና ወላጆች የተጨፈጨፉበት የሰኔ 1 ቀን 4ኛ አመት ባልፈው ሰኞ በበርካታ ኢትዮጵያዊያኖች ዘንድ ታስቦ መዋሉን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰን ዜና አረጋግጦአል።

ወያኔ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ የመረጠው ፓርቲ ሥልጣን እንዳይይዝ ለመከላከል በወሰደው እርምጃ፤ የፖሊስ፣ የደህንነትና የመከላከያ ሰራዊቱን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሥር እንዲገባ ካደረገ በኋላ፤ የሰጠሁት ድምጽ ይከበርልኝ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ በወጣው ህዝብ ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትእዛዝ መስጠቱ ይታወቃል። በዚያኑ ዕለትም የሴት ልጁን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቅ በማስመልከት በሸራተን ሆቴል በተጣለ ድግስ ያከብር እንደነበር በወቅቱ መዘገቡ ይታወቃል።

በመለስ ዜናዊ አመራር የደረሰውን የሰኔ አንድን የግፍ ጭፍጨፋ ለማስታወስ በተለያዩ የአለም ክፍሎች የተለያዩ ዝግጅቶች በመደረግ ላይ ሲሆኑ፣ የግፍ ጭፍጨፋውን በማስመልከት በአርቲስት ታማኝ በየነ ተዘጋጅቶ የቀረበው ዶክመንታሪ ፊልም የብዙዎችን አድናቆት አትርፏል። ይህ ዶክመንታሪ የመለስ ቅልብ ወታደሮች ንጹህ ኢትዮጵያውያንን ግንባር ግንባራቸውን እያሉ ሲረሽኑ የሚያሳይ ሲሆን፣ ዘረኛውንና አምባገኑን መለስ ዜናዊን ለመክሰስ ተጨማሪ ማስረጃ እንደሚሆን አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል።

## ሕግ-አልባነትን ሕጋዊ የሚያደርገውን አዋጅ መቃወም ፍትህና ነፃነትን የሚወዱ ዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው

ተቀናቃኞችን ለማጥቃትና ለዲስኩር ማሳመሪያነት ካልሆነ በስተቀር በሥራ ላይ ውሎ የማያውቀው የወያኔ ሕገ-መንግሥት በሰበብ አስባቡ ሲሸራረፍ ቆይቶ አሁን ”የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ” የተሰኘው ደራጎን ገድሎ ሊቀብረው ተዘጋጅቷል፡፡

የወያኔ መኩራሪያና ማጥቂያ ሕገ-መንግሥት ለበርካታ የሰብዓዊና የዜግነት መብቶች እውቅና የሚሰጥ ቢሆንም አንዳቸውም በሥራ ላይ ውለው አልታዩም፡፡ ይብሱኑ በተለያዩ ጊዜያት በወጡ አዋጆች የሕገ-መንግሥቱ ማራኪ አንቀፆች ሲሸረሸሩና ሲናዱ ቆይተዋል፡፡ ለአብነት ያህልም ሙስና፣ አደገኛ ቦዘኔ፣ የባንክ ብድር፣ ፕሬስ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከቱ የወጡ አዋጆችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህንና ሌሎችን ያልተዘረዘሩ አዋጆች ሕገ-መንግሥቱ እውቅና የሰጣቸውን መብቶች ሸራርፈዋል፡፡ የህጎች ሁሉ የበላይ ነው የተባለለት ሕገ-መንግስት በአዋጆችና ድንጋጌዎች ተሸርሽሮ አጥንቱ ብቻ በቀረበት ባሁኑ ወቅት እስከነአካቴዉ ገድሎ የሚቀብረው “የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ” ተረቅለት ለመጽደቅ የጣት ቆጠራ ብቻ ቀርቶታል፡፡

ይህ ህግ “ሽብርተኝነት” እና ‹”ሽብር ተግባራት” የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች የሰጠው ትርጓሜ ከመጠን በላይ በመለጠጣቸው ማናቸውም ዓይነት የፓለቲካ ተቃውሞ በሽብርተኝነት ለመፈረጅ ያስችላሉ፡፡ በዜጎች በተለይም በወጣቶች የተለመዱ የተቃውሞ መግለጫዎች ሁሉ በአዋጁ መሠረት “ሽብርተኛ” ያስብላሉ፡፡ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የሚታወቁት የተማሪዎች አድማ፣ መንገድ መዝጋት፣ ድንጋይ ውርወራ ከእንግዲህ “የሽብር ተግባራት” ይሰኛሉ፤ ከአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እስከ ሞት ድረስም ያስቀጣሉ፡፡ መለስና በረከት በኃይለሥላሴና በደርግ ጊዜ የነበራቸውን መንግሥትን የማወክ አንፃራዊ ነፃነት አንድ ሺህኛውን እንኳን ለዛሬው ወጣት ሊፈቅዱ አልፈለጉም፡፡

በቅጣት ብዛት ለማሸማቀቅም በሽብርተኛነት የተፈረጀ ድርጅት አባል መሆን ቀርቶ የሞራል ድጋፍ እንኳን መስጠት ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ተደርጓል፡፡

ይህ አዋጅ ወትሮውኑም ከፍትህ ጋር የማይተዋወቁትን የወያኔ ፍርድ ቤቶች ቅራቅቦዎችን በማስረጃነት የሚሰበስቡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ አድርጓቸዋል፡ ከእንግዲህ ፍርድ ቤቶች የስሚ-ስሚ ወሬዎችን፣ ተከሳሾችን በማሰቃየት የተገኙ ቃሎችን፣ በተጠለፉ ስልኮችና በዘረፋ የተገኙ «ማስረጃዎችን»፣ የራሳቸው የሰላዮችና የከሳሾቹ ሪፖርቶችን እና የመሳሰሉትን በአክብሮት በመመዝገብ ብይን የሚሰጥባቸው ጣቢያዎች ይሆናሉ፡፡

በዚህ አዋጅ የዜጎች ሕይወት በፓሊስ መዳፍ ውስጥ ተጥሏል፡፡ ፓሊስ በሽብርተኝነት የጠረጠረውን ሰው በማንኛውም ጊዜ ሊያስር፣ ሊፈትሽ እና ንብረቱን ሊወርስ ሥልጠን ተሰጥቶታል፡፡ ለአራት ወራት ጽኑ እስር ህጉ ከፓሊሱ የሚፈለገው ያሰረውን ሰው በየሃያ ስምንት ቀናት ወደ ፍርድ ቤት ብቅ እያደረገ ሌላ ሃያ ስምንት ቀናት የማስጨመርን «ልፋት» ብቻ ነው፡፡

ስለ ሽብር ተግባር መረጃ አለመስጠት ከሶስት እስከ አስር ዓመት ያስቀጣል፡፡ የተሳሳተ መረጃ መስጠትም እንደዚያው ከሶስት እስከ አስር ዓመት ያስቀጣል፡፡ በሌላ አነጋገር እያንዳንዱ ዜጋ መሪማሪ ፓሊስ ሆኖ ስለሚሰጠው መረጃ ትክክለኝነት ራሱ ምርመራ እንዲያደርግ ህጉ ያስገድዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መኪናም ሆነ ቤት ያከራየ ሰው የደንበኛውን ማንነት በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ለአቅራቢያው ፓሊስ እንዲያስታውቅ በማስገገደድ የግለሰብ ነፃነትን ክፉኛ ይጋፋል፡፡

ወያኔ ድሮም ቢሆን የህጋዊነትም ሆነ የይሉኝታ ለከት ኖሮት አያውቅም፡፡ አሁን ይፈቀድልኝ የሚላቸው ነገሮች ሁሉ ድሮም ሲያደርጋቸው የነበሩ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ የፈጠረው አዲስ ነገር ቢኖር ለወያኔ ህገወጥ ተግባራት ህጋዊ ሽፋንን መስጠቱ ብቻ ነው፡፡

ወያኔ ይህ አዋጅ መላውን ዜጋ በተለይም ደግሞ ተቃዋሚዎችን ያሸምቅቅልኛል ብሎ ተስፋ እንዳደረገ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ እውነታው ግን ተቃራኒው ነው፡፡ ይህ አዋጅ ከፀደቀበት እለት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ህግ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በወረቀት ላይ እናውቀው የነበረው ሕገ-መንግሥትም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡ ይህ ደግሞ ትግላችንን ወደ አንድ ከፍ ያለ እርከን ያሸጋግረዋል፡፡ በፀረ-ሽብርተኝነት ሰበብ የታወጀውን ህግ-አልባነትን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን በትግላችን ወደ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንቀይረዋለን፡፡ ሕግ የሚባል ነገር ሁሉ ጠፍቶ አገራችን በፓሊስ የምትተዳደርበትን ሥርዓት በፍፁም መቀበል አንችልም፡፡ ሕግ-አልባነትን ሕጋዊ የሚያደርገውን አዋጅ መቃወም ፍትህንና ነፃነትን የሚወዱ ዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው

### በአገሪቱ ውስጥ በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ባለሃብቶች ለወያኔ ታማኝነት ያላቸው የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ ተገለጸ

(ከገጽ 1 የዞረ)

በአዲስ አበባ ዋና ዋና የህንጻ ተቋራጭነቱን ስራ የሚሰሩት የአዜብ መስፍን ወንድሞች እና ዘመዶች መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር መሆኑ ይታወቃል። ከአመታት በፊት ቤሳ ቤስቲን የሌለው ምስኪን ካለጥረት እና ልፋት በስልጣን ላይ ካሉት ገዢዎች ጋር ስለተዛመድ ብቻ የሀገርን ሀብት ዘርፎ ከበርቴ ሲሆን እንደሚያስቆጭ ግልጽ ነው።ኒቆዲሞስ ዜናዊ የተባለው የመለስ ወንድም ለምሳሌ ወንድሙ ስልጣን ላይ ወጥቶ የኢትዮድያን ህዝብ ዘረኛ በሆነ መንገድ መምራት እና አንጡራ ሀብቱን መዝረፍ ከመጀመሩ በፊት በቃሊት ብረታብረት የሚሰራ ወዛደር እንደነበረ ይታወቃል።መለስ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ የቃሊት በብረታብረታ ቱታውን አሽቀንጥሮ የጣለው ኒቆዲሞስ፤ በብርሀን ፍጥነት በ1980ዎች ታዋቂ ከነበሩት የኮንስትራክሽን ድርጅቶች አንዱ የሆነው ጃክሮስ ኢትዮድያ ሽሪክ እንደነበረ በስፋት ይነገር እንደነበር ይታወቃል።

ከሀገሪቱ የህዝብ ቁጥር ስድስት ከመቶ ብቻ ከሆነው ዘውግ የመጣው ወያኔ ከ80 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የሚኖርባትን ምድር የእኔ የሚላቸው ሰዎች በፓለቲካ፤ በምጣኔ ሀብት እና በማህበራዊ ፍጽማዊ የበላይነት እንዲኖራቸው የሚሰራው ሀገራዊ ደባ አስተዛዚቢ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ነው ተብሏል። ስለጉዳዩ ያነጋገርናቸው ታዛቢ ወያኔ በዘር ተደራጅቶ የሚፈጽመው በደል እና ዝርፊያ ከአእምሮ በላይ ነው፤ የወያኔ አገዛዝ ወደ ታሪክ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መጣሉ አይቀሬ ነው ነገር ግን የትግራይ ህዝብ በስሙ የሚነግድበትን ወያኔን በግልጽ እና በአደባባይ “እኔን አይወክለኝም።በኢትዮድያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ አውቃለሁ።እኔም የግፉ ገፈት ቀማሽ ነኝ።ከወገኔ ጋር ሆኜ አገዛዙ እታገላሁ ማለት አለበት” ብለዋል።

እኚህ ታዛቢ ለምሳሌ ወያኔ ፈር በለቀቀ ሁኔታ በዘር ተቧድኖ የጠቀለለውን ስልጣን በደንብ ለመረዳት በሶማሊያን በወረረበት ጊዜ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን የተላለፉ ዜናዎችን መለስን ብለን እንመልከት “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሶማሊያ አክራሪዎች አከርካሪያቸው እንደተመታ አስታወቁ፤ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ስለ ሶማሊያ ጉዳይ ለምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታ ኢጋድ ገለጻ አደረጉ፤ የጦር ሀይሎች ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ሳሞራ የነሱ የመከላከያ ሰራዊቱ በሳይንሳዊ ስልጠና የተኮተኮተ ነው አሉ፤ በሶማሊያ የኢትዮድያ ጦር አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ስዩም ሀጎስ የሰራዊቱ የውጊያ ሞራል ከፍተኛ መሆኑን ለዋልታ ገለጹ፤ የሶማሊያ አክራሪዎች ለቀጣናው አለመረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽዎ እያደረጉ እንደሆነ ዶክተር ክንፈ አብርሀም የኢትዮድያ ሰላም እና ልማት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አስገነዘቡ” ይህ ኢትዮድያ ማለት በአለም ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማያቅ መንገድ በጥቂት ጎጠኞች መዳፍ ስር የወደቅች አሳዛኝ አገር መሆኗን በደንብ ያስረዳል ብለው አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

# የኢትዮጵያ የደህነት ችግሮችና መፍትሄ (ካለፈው የቀጠለ)

## 3. መፍትሄ

የኢትዮጵያ የውስጥም የውጭም የደህንነት ችግሮች በርካቶች ቢሆኑም መፍትሄዓቸው ግን አንድ ነው - **በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እና የአገሩን ጥቅም የሚያስቀድም መንግሥት መኖር**፡፡ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ስለሚያውቅ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት፣ ተቃዋሚ ፓለቲከኞችን ደግሞ እርስበርሳቸው እያናከሰ፤ ራሱንና ወዳጆቹን በሃብትና ስልጣን እያሳበጠ፤ በፓሊስ፣ በስለላና ወታደራዊ ተቋሞቹ አማካይነት ከፋፍሎ፣ ረግጦ፣ ቀጥቅጦ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ፓርቲው ኢህአዴግም ወደ ስለላ ድርጅትን ከተቀየረ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢህአዴግ አባለት ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል አንድም በጥቅም አሊያም በተፅዕኖ የተሰባሰቡ እርስ በርስ የሚጠቃቀሙና የሚሰላለሉ ሰዎች የሞሉት ድርጅት ነው።

በወያኔዋ ኢትዮጵያ ነፃ ፓርቲ፣ ነፃ ህዝባዊ ማኅበር ቀርቶ ነፃ የንግድ ድርጅት እንኳን እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ የሰላዮቹ የሙሉ ጊዜ ሥራ ነፃ ለመሆን የሚጥሩ ድርጅቶች አባላትን እርስ በእርስ ማጣላት፤ ያ ካልተቻለም ማስወገድ ነው፡፡

ወያኔ የጠበቀ ወዳጅነት ያለው በርቀት ካሉት ኃያላን የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት ጋር ነው፡፡ የእነሱን ወዳጅነት የገዛው ከአሸባሪዎች ጋር በሚያደርጉት ፍልሚያ ግንባር ቀደም ዘማች በመሆን ባሳየው ታማኝነት ነው፡፡ ይህ የፀረ-ሽብርተኝነት አጀንዳ ከተነጠቀ የእነሱ ወዳጅነት ያከትማል፡፡

የኢትዮጵያ የደህንነት ችግሮች ሁሉ መሠረታዊ መፍትሄ ወያኔን አስወድዶ በምትኩ የህዝብ ይሁንታ ያለው መንግሥት ማቋቋም ነው፡፡ የሚመሠረተው መንግሥት ከወያኔ የበለጠ የቀጠናውን ሰላም ማስጠበቅ የሚችል እንደሚሆን ለኃያላን መንግሥታት የማስረዳት የዲፕሎማሲ ሥራ መከወን ይኖርብናል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ ይሁንታና ተቀባይነት ያለው መንግሥት ከተቋቋመ ከላይ ከተዘረዘሩት የደህንነት ችግሮች ውስጥ አብዛኛዎቹ ወደ ጥንካሬ ምንጭነት ሊለወጡ ይችላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ቀጥሉ በቁጥር ከፍተኛ የሆነ የሶማሌ ዘዉጌ ማኅበረሰብ አባላት አገር ናት፡፡ የተረጋጋችና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መኖር ከኢትዮጵያ ሶማሌዎች አልፎ ለሶማሊያ ሶማሊዎችም ችግር ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ መሠረት መጣል እንድትችል እድል ይሰጣታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቁጥር ኤርትራ ካለው የሚበልጥ ትግርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩም ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለኤርትራ ሕዝብ የምትሰጠው ተግባራዊ ትምህርት የላቀ ይሆናል፡፡ የጅቡቲ ዘዉጌ ማህበረሰቦች በሙሉ መሠረታቸው ኢትዮጵያ ነዉ፡፡ ከሰሜን ምሥራቅና ደቡብ ሱዳን ጋርም ማህበረሰባዊ ዘውግ፣ ባህልና ቋንቋ ትጋራለች፡፡ ይህ ሁሉ የሚያመለክተዉ መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ ውስጥ ማስፈን ያንን ጥሩ ባህል ወደ አፍሪቃ ቀንድ አገሮች ለማሰራጨት ከሁሉም በላይ የተመቸች አገር ናት፡፡

የአፍሪቃ ቀንድ አገሮች ፌደራላዊ መንግሥት ለሚያልሙ ቅን ሰዎችም መሠረታቸው እና መነሻቸው ኢትዮጵያ መሆን ይኖርበታል፡፡ ወያኔን አስወግደን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ኢትዮጵያ ዉስጥ ካሰፈንን ህልሞቻችንን ማስፋትና ማጉላት እንችላለን፡፡ በወያኔ አገዛዝ ግን እንኳንስ የተባበረች የአፍሪካ ቀንድ ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ ኢትዮጵያም አትኖረንም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ በቁጥር ከብዙ እስላማዊ አገሮች የበለጡ ሙስሊም ዜጎች ያሏት አገር ናት፡፡ በሙስሊም ዜጎች ብዛት ኢትዮጵያ ከሳዉዲ አረቢያ፣ ከሱዳን፣ ከአፍጋኒስታንና ከኢራቅ ትበልጣለች፡፡ የሙስሊሙና የክስርቲያኑ ብዛት መሳ ለመሳ ለመሆን እየተቃረበ ነው፡፡ ሙስሊሙ የክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ደግሞ የሙስሊሙን በዓል የሚያከብርበት አገር ነው ያለን፡፡ አንድ ቤተሰብ ውስጥ ከፊሉ ክርስቲያን ከፊሉ ደግሞ ሞስሊም የሆነበት ቀየ በርካታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአግባቡ ከተያዘ ለኢትዮጵያ ትልቅ ክብር ነው፡፡ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ ተደጋግፎ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ከቻለ ለአፍሪቃ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ትልቅ ትምህርት ነው፡፡

በሃይማኖትና በዘር ከፋፍሎ ከሚያፋጅን ወያኔ ተገላግለን ከአፍሪቃ ቀንድ አልፎ ለመላው ዓለም አርዓያ የመሆንን ምቹ የታሪክ አጋጣሚ ማሳለፍ ፈጽሞ የለብንም፡፡

## 4. ማጠቃለያ

ይህ አጭር ጽሁፍ የኢትዮጵያ የደህንነት ችግሮችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ለይቶ ለመተንተን ሞክሯል፡፡

ድህነትና ኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፤ ማህበራዊ ዘዉግና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች መበራከት፤ እና በተቋማት ላይ እምነት ማጣት በውስጥ ችግሮቻችን ምንጭነት ተወስተዋል፡፡ ከአካባቢው አገሮች ጋር ያለን ግኙኝነት የሻከረ መሆኑ ደግሞ የውጭ የደህንነት ችግሮቻችን ምንጮች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

ለኢትዮጵያ የደህንነት ችግሮች አንድ አጠቃላይ መፍትሄ ቀርቧል - ወያኔን አስወግዶ በምትኩ የሕዝብ ይሁንታ ያለው፤ የአገሪቱን ጥቅም የሚያስቀድም መንግሥት ማቋቋም፡፡

በሕዝብ ፈቃደኝነት ሥልጣን የያዘ፤ አገራዊ ራዕይ ያለው መንግሥት ኢትዮጵ ውስጥ እንዲኖር ከተደረገ ዛሬ በችግርነት በተወሱት ውስጥ አብዛዎቹ የችግር ሳይሆን የጥንካሬ ምንጭ ይሆናሉ፡፡

በርካታ ኢትዮጵዊያን ሶማሊዎች መኖራቸው ከራሳችን አልፎ ለሶማሊያ ሶማሊዎችም የመፍትሄ አቅጣጫ ጠቋሚ መሆን እንችላለን፡፡ለኤርትራዊያንም ለጅቡቲያዊንም ከኛ የቀረበ ወዳጅ አይኖራቸውም፡፡ ከሰሜን-ምሥራቅና ደቡብ ሱዳንም ጋር እንዛመዳለን፡፡ ኢትዮጵያ ፍትህና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ለአፍሪቃ ቀንድ አገሮች የጠነከረ ትብብር - ለምሳሌ ኮንፌዴሬሽን - መሠረት መሆን ትችላለች፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከብዙ እስላማዊ አገሮች የበለጠ የሞስሊሞች አገር ናት፡፡ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በሃይማኖቶች እኩልነትና መቻቻል ረገድ ለዓለም ልታበረክተው የሚቻላት አርዓያነት አለ፡፡

የዚህ ሁሉ መቋጫው ግን መንግሥት ነው፡፡ ወያኔ በታኝ ኃይል ነው፡፡ በወያኔ አስተዳደር የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም መፍትሄው ይህን ጠባብና ዘረኛ መንግሥት አስወግዶ በምትኩ በሕዝብ ይሁንታ ያገኘ፣ እኩልነትንና ፍትህን ማስፈን የሚችል መንግሥት መመሥረት ነው፡፡ ይህ የአገራችን ደህንነት ቁልፍ መፍትሄ ነው፡፡ ከዚህ ተነስተን ነው ስለ አፍሪቃ ቀንድም ሆነ ስአፍሪቃ ኀብረት ማለም የምንችለው፡፡

ወያኔን ማስወደግ በዚህ ትውልድ ላይ የተጣለ የታሪክ እዳ ነው፡፡ ይህ እዳ በቆየ መጠን ተጨማሪ እዳ ይወልዳልና በፍጥነት ሊወገድ ይገባዋል። ይህ ደግሞ በአንድ ድርጅት የተናጠል አልያም በተለያዩ ድርጅቶች የተነጣጠለ ትግል የሚሆን አይደለም። ይህ ትግል የነ መለስን ጠባብና ዘረኛ መንግስት አስወግዶ በምትኩ የህዝብን ይሁንታ ያገኘ መንግስት የመገንባት እና ዜጎቿ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበረባት እኩልነትና ፍትህን የህልውናዋ የማዕዘን ድንጋይ ያደረገች ከራሷ አልፋ ለጎረቤቶቿ ተምሳሌት የምትሆን ለዜጎቿ የኩራት ምንጭ የሆነች አገር የመፍጠር ራዕይ ሰንቀው የሚጓዙ ድርጅቶችን ሁሉ የተቀናጀ ትግል ይጠይቃል። አገራችን አሁን ያለችበት ጊዜ ደግሞ ያ መቀናጀት ዛሬውኑ ይወለድ ይላል። ነገ ሊረፍድ ይችላልና።

## በመንግስት ግልበጣ የተያዙት 46 ሰዎች ባለሥልጣኖችን በመግደል ሙከራ ተከሰሱ (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ ሃሙስ ግንቦት 27 ቀን 2001 በውጭ አገር እንደሚኖሩ ከተጥቀሱ አስራ ሁለቱ ተከሳሾች በስተቀር ስማቸው ለህዝብ ይፋ ያልተደረጉ 46 ሰዎች በወያኔ ፍርድ ቤት በግድያ ሙከራ ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑን ቃላ አቀባዩ በረከት ስሞን ከሰጠው መግለጫ ለማወቅ ተችሎአል። ወያኔ ክስ ከመሰረታቸው አሥራ ሁለቱ የውጭ ነዋሪዎች 6ቱ የግንቦት 7 አመራር አባላት ሲሆኑ ሁለቱ የቀድሞ የነጻው ፕሬስ አባላት የነበሩና በምርጫ 97 ወቅት ያለጥፋታቸው ወህኒ ወርደው የወያኔን የግፍ መከራ የተቀበሉ መሆናቸው ታውቆአል ።

ባለፉት አምስት ሳምንታት ውስጥ፥ የሃሰት ምስክሮች እና ለሙያቸው ሳይሆን ለጥቅማ ጥቅም የሚገዙ ጠበቃዎች በሚመላለሱበት፣ የአገዛዙ መጫወቻ ሜዳ ወደሆነው ፍርድ ቤት ለአራት ጊዜ የተመላለሱት እስረኞች፤ ተደብድበው ሰውነታቸው በመተልተሉ ቤተሰቦቻቸው እና ጠበቆቻቸው እንዳይጎበኟቸው መደረጉን መዘገባችን ይታወሳል።

ባለፈው አንድ የውጭ አገር ጋዜጠኛ በጥቅም አዕምሮአቸው ተሰልቦ ለወያኔ አገዛዝ ሽር ጉድ እያሉ ከሚገኙት አንዱ ለሆነው ሽመልስ ከማል ባቀረበው ጥያቄ እስረኞቹ በቤተሰቦቻቸው መጎብኘት ለምን እንደተከለከሉ ሲጠይቀው፣ የሚጠይቃቸው ስለጠፋ እንጂ ተከልክሎ እንዳልሆነ መናገሩ እና ቅጥፈቱ ብዙም ሳይቆይ በእስረኞቹ ዘመዶች መጋለጡ ይታወቃል። ከትናንትና በስቲያ ደግሞ የአገዛዙ የቅጥፈት አለቃ የሆነው በረከት ስምኦን፣ ሰዎቹ በማንም እንዳይታዩ የተከለከሉት የተከሰሱበት ወንጀል ሽብርተኝነት በመሆኑ እንደሆነ፤ እንዲሁም በሽብርተኝነት ተጠርጥረው የታሰሩ ሰዎችን ፖሊስ ክስ ከመመሥረቱ በፊት ለፈለገው ያህል አስሮ እንዲያቆይ የሚፈቅድ ህግ አለ ሲል ለአለም አቀፍ የዜና አውታሮች ተናግሯል። የመለስ አገዛዝ በህግ አክባሪነት የሚታወቅ ባይሆንም እንኳ፣ በረከት ውሸቱን ለመደበቅ ሲል ገና ያልጸደቀ ህግ ባደባባይ መጥቀሱ የሰዎቹ የውሸት ካብ ከመርዘሙ የተነሳ እራሳቸው እንኳ ደርሰውበት መቆጣጠር እንደተሳናቸው ያሳያል ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

በተለይ በጦሩ ውስጥ አድሏዊነትን እና ዘረኛነትን በሚመለከት እየተነሱ ካሉት ተቃውሞዎች የተነሳ ከፍተኛ ሽብር ወስጥ የገባው ወያኔ ከያዘው ብርክ ማገገም አቅቶት፤ ከድሃው ህዝባችን ጉሮሮ እየተመነተፈ የሚሰጣቸውን ከልክ ያለፈ ገንዘብ እየበሉ ስራቸው ውሸት ማምረት ብቻ የሆነው ባለሟሎቹ እንኳ ቅጥፈታቸውን መደበቅ እየተሳናቸው መጥቷል።

እስረኞቹ በፍርድ ቤት ሊገጥማቸው ስለሚችለው ሆኔታ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪ፥ የቅንጅት አመራሮች በተፈበረከው ክስ ከቃሊቲ እስር ቤት በሚመላለሱበት ወቅት የተከሰትውን አንድ ዝነኛ ገጠመኝ በመጥቀስ፣ ይህ የወያኔ የፍርድ ሂደት የሃሰት ምስክሮች እና የተፈበረኩ ማስረጃዎች የሞሉበት እንደሚሆን ጥርጣሬ እንደሌላቸው ገልጸዋል። በዛን ወቅት ሽመልስ ከማል አሰልጥኖ ለሃሰት ምስክርነት እንዲቀርቡ ያደረጋቸው ኑር ሃሰን የተባሉ ሰው ፍርድ ቤት ቀርበው ምንም እንደማያውቁና ታሪኩን እንዲናገሩ ያዘዛቸው አቃቤ ህግ መሆኑን ማጋለጣቸው ይታወሳል።

## በአገሪቱ ውስጥ በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ባለሃብቶች ለወያኔ ታማኝነት ያላቸው የትግራይ ተወላጆች (ክገጽ 1 የዝረ)

በአዲስ አበባ ዋና ዋና የህንጻ ተቋራጭነቱን ስራ የሚሰሩት የአዜብ መስፍን ወንድሞች እና ዘመዶች መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር መሆኑ ይታወቃል። ከአመታት በፊት ቤሳ ቤስቲን የሌለው ምስኪን ካለጥረት እና ልፋት በስልጣን ላይ ካሉት ገዢዎች ጋር ስለተዛመድ ብቻ የሀገርን ሀብት ዘርፎ ከበርቴ ሲሆን እንደሚያስቆጭ ግልጽ ነው።ቃሊቲ ብረታ ብረት ወዛደር የነበረው ኒቆዲሞስ ዜናዊ የተባለው የመለስ ወንድም፤ ወንድሙ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ በብርሀን ፍጥነት በ1980ዎች ታዋቂ ከነበሩት የኮንስትራክሽን ድርጅቶች አንዱ የሆነው ጃክሮስ ኢትዮጵያ ሽሪክ እንደነበረ በስፋት ይነገር እንደነበር ይታወቃል።

ከሀገሪቱ የህዝብ ቁጥር ስድስት ከመቶ ብቻ ከሆነው ዘውግ የመጣው ወያኔ ከ80 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የሚኖርባትን ምድር የእኔ የሚላቸው ሰዎች በፓለቲካ፤ በምጣኔ ሀብት እና በማህበራዊ ፍጽማዊ የበላይነት እንዲኖራቸው የሚሰራው ሀገራዊ ደባ አስተዛዚቢ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል ነው ተብሏል።

ታዛቢወች ወያኔ በዘር ተደራጅቶ የሚፈጽመው በደል እና ዝርፊያ ከአእምሮ በላይ ነው፤ የወያኔ አገዛዝ ወደ ታሪክ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መጣሉ አይቀሬ ነው ነገር ግን የትግራይ ህዝብ በስሙ የሚነግድበትን ወያኔን በግልጽ እና በአደባባይ “እኔን አይወክለኝም።በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ አውቃለሁ።እኔም የግፉ ገፈት ቀማሽ ነኝ።ከወገኔ ጋር ሆኜ አገዛዙ እታገላሁ ማለት አለበት” ብለዋል።

እኚህ ታዛቢ ለምሳሌ ወያኔ ፈር በለቀቀ ሁኔታ በዘር ተቧድኖ የጠቀለለውን ስልጣን በደንብ ለመረዳት በሶማሊያን በወረረበት ጊዜ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን የተላለፉ ዜናዎችን መለስን ብለን እንመልከት “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሶማሊያ አክራሪዎች አከርካሪያቸው እንደተመታ አስታወቁ፤ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ስለ ሶማሊያ ጉዳይ ለምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታ ኢጋድ ገለጻ አደረጉ፤ የጦር ሀይሎች ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ሳሞራ የነሱ የመከላከያ ሰራዊቱ በሳይንሳዊ ስልጠና የተኮተኮተ ነው አሉ፤ በሶማሊያ የኢትዮጵያ ጦር አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ስዩም ሀጎስ የሰራዊቱ የውጊያ ሞራል ከፍተኛ መሆኑን ለዋልታ ገለጹ፤ የሶማሊያ አክራሪዎች ለቀጣናው አለመረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽዎ እያደረጉ እንደሆነ ዶክተር ክንፈ አብርሀም የኢትዮጵያ ሰላም እና ልማት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አስገነዘቡ” ይህ ኢትዮጵያ ማለት በአለም ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማያቅ መንገድ በጥቂት ጎጠኞች መዳፍ ስር የወደቅች አሳዛኝ አገር መሆኗን በደንብ ያስረዳል ብለው አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## አሸባሪ የሆነው የነመለስ ቡድን በፀረ-ሽብር ሽፋን ያረቀቀው “አሸባሪ ህግ” ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው (ክገጽ 1 የዞረ)

""ሕዝቦቿ በልተው ማደር በማይችሉባት ድሀ አገር፥ የሰው ትከሻ ሊሸከመው በማይችል ሁኔታ ሕገ መንግሥቱን ጥሶ የሰዎች ቤት እንዲመረመር እና ሰው ከመቅጽበት እንዲፈተሽ መጠየቅ አስፈላጊ አይመስለኝም" ያሉት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት ተወካይ አቶ ገብሩ ገብረማርያም፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የወንጀል ሕጐችን በመጠቀም ሽብርተኝነትን ስትከላከል የቆየች በመሆኗ አሁን የተዘጋጀው ዐይነት ረቂቅ የጸረ-ሽብርተኝነት ሕግ መተግበር እንደማያስፈልጋት አስረድተዋል።.

ሌላው የህብረት ተወካይ አቶ ወንድሙ ኢብሳ በበኩላቸው ረቂቅ ህግ ተብየው ለአስፈጻሚ አካል የተለየ ስልጣን የሚሰጥና የዜጐችን መብት ክፉኛ የሚጥስ በመሆኑ አጥብቀው እንደሚቃወሙት ተናግረዋል፡፡ “እንደውም ረቂቅ አዋጁ ራሱ ሽብር ነው" በማለት አስረድተውዋል። በትክክል ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያስፈልገው፣ የሕዝብ ቅንነትና ትብብር እንጂ የአስፈጻሚ አካልን ጡንቻ ማዳበር አይደለም ብለዋል፡፡

ረቂቅ ህግ ተብየው ዜጎች ለነፃነት የሚያደርጉትን የትጥቅ ትግል ከሽብር ለመፈረጅ መሞከሩም፤ በዓለም ላይ ያልታየ፣ ከጭንቀት የተፃፈና ሰሚ የማያገኝ ባዶ ጩኸት መሆኑንም ተቃዋሚዎቹ አልሸሸጉም። ሌላው ጠቃዋሚ አቶ ብሩ በርመጃን ረቂቁ የዜጎችን ነፃነት በሁሉም አቅጣጫ የሚጥስ መሆኑን በማውሳት፤ “ይህ ህግ ከፀደቀ ምን ዓይነት አገር ውስጥ ነው ያለነው? የሚያሰኝ ይሆናል” ብለዋል።

በአፋኙ ፓርላማ በመቅኑን ተለክታ በተሰጠቻቸው ሁለት ደቂቃ የአደራ ተማፅኗቸውንና ጥሪያቸውን በከፍተኛ ሀይለ ቃል ያሰሙት የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ "**ይህ ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ በግራም በቀኝም በዚህ ምክር ቤት ውስጥ የተቀመጥን ሰዎች ይህንን ሕግ መቃወም አለብን፣ ምክንያቱም አገራችንን ለአምባገነኖች፣ ለጐበዝ አለቆችና ለፖሊስ ልናስረክብ ነው**" በማለት ነው ጥሪያቸውን ኣስተጋብተዋል።

ረቂቅ ሕጉ አስፈፃሚውን ወደ ፖሊስነት፣ አምባገነንነትና ወደ ጐበዝ አለቅነት የሚወስድ ነው ያሉት አቶ ቡልቻ፣ ረቂቅ ሕጉ ካለፈ የነፃነት ጭላንጭል ከነ አካቴው ስለሚያከትም፤ ይህንን ረቂቅ ሕግ በመደገፍ ድምጽ የሚሰጡ የፓርላማ አባላት አንድ ቀን "እንዴት ድምጽ ሰጠህ?" ተብለው መጠየቃቸው እንደማይቀር ተናግረዋል፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎችና ሌሎች ዓለማቀፍ ተሰሚነት ያላቸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች በበኩላቸው፤ ረቂቅ ህግ ተብየው ከዓለማቀፍ የፀረ-ሽብርተኝነት ሰነዶችና አዋጆች ጋር ሲነፃፀር እጅግ የከፋና ደረጃ የማያሟላ በመሆኑ የመለስ አገዛዝ ይህን ሰነድ እንዳያፀድቀው ኣሳስበዋል

ስር የሰደደን ህዝባዊ ተቃውሞና እየተጋጋመ የመጣን አገራዊ ቁጣ በምንም ተዓምር ማቆም እንደማይቻል ሳይታለም የተፈታ ሀቅ ሆኖ ሳለ፤ የመለስ አገዛዝ በዕፅ ጉልበትና በተወላገደ መለኪያ፤ የዚህ አይነት ዓለምን ያስገረመ ዕውር ሰነድ ማዘጋጀቱ ብዙዎችን ፈገግ ከማሰኘት አልፎ፡- “የጨነቀው ነፍሰ-ጡር ያገባል” የሚል ስላቅ አትርፏል።

በርካታ የፖለቲካ ሰዎች ሲናገሩ እንደሚደመጡት፤ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ሌላው ቢቀር የተፃፈበትን ያህል ዋጋ ማውጣት አልቻለም።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org